ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

ቀን፤ አርብ ሃምሌ 4 2000 ዓ.ም

የዜና ርዕስ፤ ምስራቅ አፍሪካ በአደገኛ የጦርነት ምስቅልቅል ውስጥ ሊገባ ነው

በቋፍ ላይ የሚገኘው የምስራቅ አፍሪካ ሰላም ሙሉ በሙሉ ሊደፈርስ መቃረቡን የፖለቲካ ተንታኞች በመግለጽ ላይ ናቸው። ከጥቂት ቀናት በፊት የሱዳን ባለስልጣናትን በአለማቀፍ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የሚጠይቀው ዜና ከውስጥ ምንጮች ከደረሰን በሁዋላ ባሰባሰብነው መረጃ መሰረት፣ የምስራቅ አፍሪካን ሰላም ሙሉ በሙሉ ወደ ጦርነት ሊለውጡ የሚችሉ ክስተቶች በመታየት ላይ ናቸው። ፕሬዝዳንት አልበሽርን ጨምሮ፣ ሌሎች የሱዳን ባለስልጣናትን በዘር ማጥፋትና በሰብአዊ እልቂት ለመክሰስ የሚያስችል የማሰሪያ ወረቀት ለማውጣት  ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ ባለበት በአሁኑ ጊዜ፣ የአገሪቱ ተቃዋሚዎች ደግሞ የሱዳን ዋና ከተማ የሆነችውን ካርቱምን ለመያዝ ዝግጅታቸውን በማጠናቀቅ ላይ ናቸው።ተቃዋሚዎቹ በካርቱም ላይ የሚያደርሱት ጥቃት ከፍተኛ የሆነ ሰብአዊ ቀውስ ሊፈጥር እንደሚችል ተንታኞች እየተናገሩ ሲሆን፣ በተባበሩት መንግስታት እና በሌሎች አለማቀፍ ድርጅቶች የሚሰሩ የውጭ አገር ዜጎች ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ሰሞኑን መልእክት በእየድርጅቶቻቸው በኩል ተላልፎላቸዋል። በተለይ የፕሬዝዳንቱ የመከሰስ ዜና በውጭ አገር ዜጎች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ሊያባብሰው ይችላል የሚል ፍርሀት ሲኖር፣ በሱዳን መንግስትና፣በተቃዋሚዎች መካከል የሚደረገውን ድርድር ሊያሰናክለው ይችላል ተብሎም ይታመናል።

በሱዳን የሚፈጠረው ጦርነት ወደ ጎረቤት አገሮችም ሊዛመት እንደሚችል ተንታኞች እየተናገሩ ሲሆን በቅርቡ በኢትዮጵያ እና በሱዳን መካከል ተፈጠረ የተባለው ውዝግብ ከዚህ ጋር አብሮ ሊታይ ይችላል ይላሉ። የአሜሪካ የደህንነት ሀይል በሱዳን ውስጥ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የሱዳንን ባለስልጣናት እያስቆጣ ሲሆን፣ የአሜሪካን ፖሊሲዎች በማስፈጸም ላይ ያለው የወያኔ መንግስት የሱዳን ጦር በኢትዮጵያ ድንበሮች አካባቢ ሀይሉን እንዲያከማችና ለአማጽያኑ ጥቃት የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር እንዲረዳው ግጭቶችን በመለኮስ ላይ መገኘቱ፣ በአሜሪካ  የተሸረበ ሴራ ሳይሆን እንደማይቀር ይናገራሉ። ወያኔ የያዘው አቋም ከሱዳን ጋር የኢትዮጵያን ግዛት በመሸጥ ከሚያገኘው ጥቅም የበለጠ ለአሜሪካን እሽክርና በመቆም የሚገኘው ጠቅም ይበልጣል የሚል ስሌት አለበት ተብሎ ይገመታል፡፡ እነዚህ ተንታኞች እንደሚሉት ምናልባት የአልበሽር መንግስት የአማጽያኑን ጥቃት መቋቋም ከቻለ፣ ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ የሚያዞርበት እድል እንዳለ ታሪክን አጣቅሰው ይናገራሉ።የግብጽ ጦር በሱዳን መሃዲስቶች በተከበበት ወቅት፣የእንግሊዝ ልኡክ የነበረው ፣አድሚራል ህይወት  ከአጼ ዮሀንስጋር በ1873 ተደራድሮ  ግብጾች በኢትዮጵያ በኩል እንዲያመልጡ ካስደረገ  በሁዋላ፣ አጼ ዮሀንስን ዞር በሉ ማለቱ ሱዳን ውስጥ እንደተሰማ፣ በኢትዮጵያኖች ሴራ የተበሳጬት መሀዲስቶች ጥቃት በማድረስ ንጉሱን እስከመግደል መድረሳቸው ይታወቃል። እንደሚጠረጠረው በተመሳሳይም የአሜሪካ አሽከር በመሆን የአካባቢውን ሰላም በማደፍረስ ለይ ያለውን የወያኔን አገዛዝ ለመምታት፣  የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች በሱዳን ውስጥ እንዲደራጁ ልትፈቅድ ትችላለች ተብሏል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፣ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች በሱዳን ቦታ እንዳያገኙ ለሱዳን መሬት በመስጠትና በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች ለመያዝ ጥረት ሲያደርግ የቆየ ቢሆንም፣ በአጭር ግዜ ውስጥ ተገልብጦ የአልበሽርን መንግስት ለማዳከም ከአሜሪካኖች ጋር ሊያሴር ይችላል ብለው ባያምኑም ይህ እንዳሻው መገለባበጥ የለመደ አገዛዝ የሚሳነው ነገር የለም የሚል ግምት አለ፡፡

የአሜሪካኖች የሱዳንን የነዳጅ ቧንቧዎች የመቆጣጠር እንቅስቃሴ፣ ለሱዳን ተቃዋሚዎች መጠንከር አስተዋጽኦ እያደረገ ሲሆን፣ በሱዳን ነዳጅ በማውጣት ላይ ላለችው ቻይና ዜናው መጥፎና አገሪቱንም ፍጥጫ ውስጥ ሊጥላት እንደሚችል ግምታቸውን ያቀርባሉ። የመለስ አገዛዝ ከአሜሪካ ጋር ሲኳረፍ ፊቱን ወደ ቻይና በማዞር በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የነበረውን የመገለባበጥ ዲፕሎማሲ በመተግበር ላይ ሲሆን፣ አዲሱ ክስተት ግን ከቻይናውያን ጋር ግጭት ውስጥ ሊከተው እንደሚችል ይገመታል።
ሱዳን ከኤርትሪያ ጋር ስምምነት በመፍጠር በወያኔ ላይ የእጅ አዙር ጥቃት ልትፈጽም እንደምትችል ተንታኞች አክለው ይናገራሉ። የመለስ ዜናዊ ጦር በሶማሊያ፣ በኦጋዴን፣ በጎንደርና በኦሮሚያ በመደረግ ላይ ባሉ ጦርነቶች ተወጥሮ በተያዘበት ወቅት፣ አዲስ ጦርነት በሱዳንና በኤርትሪያ በኩል ከተከፈተ፣ አገሪቱን ሊበታትናት እንደሚችል ስጋታቸውን ይገልጻሉ።

በሌላ በኩል የግንቦት ሰባትን አመራር ጨምሮ ያነጋገርናቸው የጥቂት ፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች እንደሚሉት በወያኔ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ስልጣንን ከማቆት ጋር መታየት አለበት ይላሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት ወያኔ በሱዳን በኩል የሚያደርሰው ትንኮሳ፣ በቅርቡ መሬት ለሱዳን መስጠቱን ተከትሎ እየተፈጠረ ያለውን ውጫዊና ውስጣዊ ተቃውሞ ለማለዘብ በማሰብ ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ የሱዳን ቀውስ በኢትዮጵያ ላይ የሚቀሰቅሰውን አደገኛ ሁኔታ ለመቋቋም በየግዜው ወያኔና ሌሎች የሃገራችንን በጎ የማይመኙ ሃይሎች የሚጥሉልን ማለቂያ የሌላቸው አጀንዳዎች አንጠልጥለን በመጭዋጭዋህ ሳይሆን በጋራ ብሄራዊ አንድነትን፣ ደህንነትንና ጥቅምን ለመከላከል በሚያስችል አጀንዳ ላይ ሁሉም ሃገር ወዳድ ሃይሎች በርትተው በጋራ ሲሰሩ ነው ይላሉ፡፡